የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት
ETHIOPIAN CIVIL SOCIETY ORGANIZATIONS COUNCIL

ቁጥር/Ref.No: ECSOC 361/22
ቀን/Date December 27/2022

# Press Release

**The Ethiopian Civil Society Organizations Council commends the efforts being made to put an end to the armed conflict in the northern part of the country as well as to implement the peace agreement. In line with this, the Council expresses its confidence that the visit made by a high-level delegation of the Federal Government to Mekele is another milestone contributing to the successful implementation of the peace process.**

Addis Abeba, December 27, 2022 - A delegation of senior government officials led by the Speaker of the House of People's Representatives,, Tagesse Chafo paid a visit to Mekele on December 26, 2022. This is the first time federal government officials are visiting Mekele since the resurgence of the armed conflict in the Northern part of the Country.

The Ethiopian Civil Society Organizations Council believes that the visit to Mekele by senior government officials indicates the progress of the implementation of the peace agreement and the continuation of the initiative to end the armed conflict in the region.

In this regard, the Council would like to recognize that the steps taken are of great importance to all affected by the conflict in repairing social cohesion and returning people affected by the conflict to their normal lives.

(251) 11 853 2005/8/9
Email: ECSOC22@gmail.com
URL:www.ecsoc.net
@ethiopian.cso_council
@Eth_CSO_Council
@ethiopian_cso_council
Ethiopian Civil Society Organizations Council
Location: Left flank, 3rd floor, Hibr Building of Hibret Bank, Addis Ababa Ethiopia

In connection with this, the Council also applauds the encouraging steps taken towards the restoration of public services such as electricity, telephone, and Banking in parts of Tigray. The Council believes that these are positive steps necessary to fulfill the basic needs of citizens and contribute to the sustenance of the peace agreement.

Finally, the Council stresses that all parties should work diligently to ensure that the peace agreement is implemented in good faith and in the interests of the country and the people of Ethiopia.

***About the Ethiopian Civil Society Organizations Council (ECSOC)***

*The Ethiopian Civil Society Organizations Council is established in accordance with Article 85 of Proclamation No. 1113/2019 and is mandated to operate in Ethiopia on behalf of all recognized civil society organizations. Currently, nearly 4,000 civil society organizations are members of the council.*

የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት
ETHIOPIAN CIVIL SOCIETY ORGANIZATIONS COUNCIL

ቁጥር/Ref.No: ኢ.ሲ.ማ.ድ.ም/ቤ7 ፎ6/15
ቀን/Date ታህሣሥ 17/2015 ዓ.ም.

# መግለጫ

**የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በሰሜኑ የሃገራችን ክፍል ተከስቶ የነበረውን የትጥቅ ግጭት ለማስቆም እና ሰላምን ለማስፈን የተደረገውን ስምምነት ለመተግበር እየተደረጉ ያሉትን ጥረቶች በእጅጉ ያደንቃል። ከዚህም ጋር ተያይዞ የፌደራል መንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት በመቀሌ ያካሄዱት ጉብኝት ለሰላም ስምምነቱ ስኬታማነት አስተዋጽዖ እንደሚኖረው የምክር ቤቱ ሙሉ እምነት ነው**

*አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፡ ታህሳስ 18 2015 ዓ.ም፦* በኢፌዲሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባዔ አቶ ታገሰ ጫፎ የተመራ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ቡድን ታህሳስ 17፤ 2015 ዓ.ም. በመቀሌ በመገኘት ጉብኝት አድርጓል። በዚህም ከትጥቅ ግጭቱ መከሰት ወዲህ የፌዴራል መንግስት ባለስልጣናት ቡድን መቀሌን ሲጎበኝ የመጀመሪያው መሆኑ ነው።

የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት የመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት የመቀሌ ጉዞ የሰላም ስምምነቱ አፈጻጸም በመልካም ሂደት ላይ እንደሚገኝ አመላካች ከመሆኑም በላይ ለሁለት ዓመት የተካሄደውን የትጥቅ ግጭት በሰላም ለማጠናቀቅ በሁለቱም ወገኖች በኩል ያለውን ተነሳሽነት ማሳያ ነው።

የተወሰደው አበረታች እርምጃ ማኅበራዊ ትስስርን በመጠገንና በግጭቱ የተጎዳውን ህዝባችንን ወደ መደበኛ ህይወቱ ለመመለስ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን እንገነዘባለን።

በተያያዘም የፕሮቶሪያው የሰላም ስምምነት ከተፈረመ በኋላ በተከታታይ እየተወሰዱ ያሉ ተስፋ ሰጭ እርምጃዎች ይበልጥ መተማመንን በማዳበር ለስምምነቱ አተገባበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ

እያበረከቱ እንደሚገኙ እንረዳለን። በዚህም ተቋርጠው የነበሩ የህዝብ አገልግሎቶች ማለትም የመብራት፣ በከፊል የስልክ እና የባንክ አገልግሎቶች መጀመር የዜጎችን መሰረታዊ ፍላጎቶች ከማሟላታቸው በተጨማሪ ለስምምነቱ ዘላቂነት ወሳኝ እርምጃዎች ሆነው አግኝተናቸዋል። በመሆኑም እነዚህ ጅምሮች ተጠናክረው እንዲቀጥሉና ሌሎች ተጨማሪ መተማመንን የሚገነቡ በጎ እርምጃዎች እንዲውሰዱ ጥሪ እናቀርባለን።

በመጨረሻም ምክር ቤቱ የተጀመረው የሰላም ስምምነት አፈጻጸም በቅን ልቦናና የሃገርንና የህዝብን ተጠቃሚነት ባስቀደመ መንገድ እንዲጠናቀቅ ሁሉም በትኩረት መስራት እንደሚገባው እያስገነዘበ ለሰላም ስምምነቱ ትግበራ የሚጠበቅበትን ሁሉ ለመወጣት ዝግጁ መሆኑን ይገልጻል።

***<u>ስለ የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት</u>***

*የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 1113/2011 በአንቀጽ 85 መሰረት የተቋቋመ ምክር ቤት ሲሆን ህጋዊ ዕውቅና ያገኙትን የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሙሉ በመወከል በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲንቀሳቀስ በአዋጁ ኃላፊነት ተሰጥቶታል። በአሁኑ ወቅትም ወደ 4000 የሚጠጉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የምክር ቤቱ አባላት ናቸው።*